# አኑርልን ገነት!

**የ**ሙዚቃው ንጉሥ ጥላሁን ገሠሠ፣
**ጥ**ሎን ኮበለለ እንባ እያፋሰሰ
**ላ**ናየው ላያየን አመለጠን ድንገት፣
**ሁ**ሉን እርግፍ አርጎ በፋሲካ ሌሊት
**ን**ብረትና ሀብቱ ህዝብ ነበር ለሱ፣
**ገ**ንዘብና ጌጡ መከዳ ትራሱ
**ሰ**ናይ ምግባር ይዞ አብሮን እንዳልኖረ፣
**ሰ**ው መሆን ከንቱ ነው ጥሎን ተሰወረ
**ን**ገሩ ለሁሉም የንጉሡን መርቅ፣
**ነ**ገ ዛሬ አትበሉ ሀገር ህዝቡ ይወቅ
**ፍ**ለጋ አይወጣ ከኡኡታ በቀር፣
**ስ**መ ጥሩው ዘፋኝ አመለጠ ከምድር
**ይ**ወደስ ይደነቅ ታምረኛ ድምፁ፣
**ማ**ራኪ ቁመናው አይነግቡ ገጹ
**ር**ቱዕ አንደበቱ ታጥቷል እንደዘበት፣
**ል**ዑል አምላካችን የዓለም ባለቤት፣
**ን**ጉሥ ጥላሁንን አኑርልን ገነት!


ማትያስ ከተማ ( welelaye2@yahoo.com )

ሚያዝያ 12 ቀን 2001 ዓ.ም.
(April 20, 2009)


http://www.EthiopiaZare.com